መልእክት አሥራ ሁለት

**እንደ የሕይወት ከተማ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም ለመሆን**
**በሕይወት በመንገሥ ድል ነሺ ኑሮ መኖር**

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ፡- ሮሜ 5፡10፣ 17፣21፤ 14፡17-18፤
ማር. 4፡26-29፤ ሉቃ. 17፡21፤ ማቴ. 24፡14

**I. እውነተኛው የክርስቲያን ሕይወት የድል ነሺ ሕይወት ነው፣ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ያሉ ድል ነሺዎች በሙሉ የጸጋን ብዛትና የጽድቅ ስጦታን ብዛት የተቀበሉ ነገሥታት መሆን አለባቸው—ሮሜ 5፡17፡-**

ሀ. በእግዚአብሔር እንደተወሰኑ ነቢያት እና ካህናት፣ እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ እና በእኛ በኩል ጠላቶቹን ሁሉ እንዲገዛ ነገሥታትም ጭምር ነን፤ በአዲስ ኪዳን ያሉ አማኞች በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ውስጥ የነገሥታት፣ የካህናት እና የነቢያት ምሳሌ መፈጸም መሆን አለባቸው፡-

1. በአዲስ ኪዳን ውስጥ አማኞች በሙሉ ነገሥታት እና ካህናት ለመሆን ድነዋል፤ ካህናት ለእግዚአብሔር ሲናገሩ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ፣ የእግዚአብሔር ንግግር ይሆናሉ፣ እነዚህም ነቢያት ናቸው—1 ጴጥ. 2፡5፣ 9፤ ራእ. 1፡6፤ 20፡6፤ 22፡3-5፤ 1 ቆሮ. 14፡12፣ 24-25፣ 31።
2. ትንቢት መናገር (ክርስቶስን ወደ ሰዎች ውስጥ መናገር) ድል ነሺዎች ያደርገናል፤ ትንቢት መናገር የድል ነሺዎች አገልግሎት ነው—ቁ. 4፤ 1 ጴጥ. 4፡10-11፤ ሐዋ. 5፡20 እና የግርጌ ማስታወሻ 2።

ለ. በክርስቲያን ሕይወታችን የንጉሥነት ደረጃ ላይ ካልደረስን አሁንም ተገቢ ከሆነው ደረጃ በታች ነን፤ ክርስቶስን እንደሰታለን ልንል እንችላለን፣ ነገር ግን እስከየትኛው ደረጃ ድረስ፣ እስከየትኛው መጠን ድረስ ነው ክርስቶስን የምንደሰተው?

ሐ. የክርስቶስ ድሰታችን "የአንድ ኢንች ከፍታ" ብቻ ያለው ሊሆን ይችላል፣ ክርስቶስ ግን አይወሰንም፤ የክርስቶስ ድሰታችን ወደ ንግሥና ደረጃ መድረስ አለበት፤ ልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ጸጋ ደጋግ መጋቢዎች መሆን እንችል ዘንድ ጸጋ በውስጣችን መንገሥ እስከሚችልበት መጠን ድረስ በጸጋ ላይ ጸጋ መቀበል ያስፈልገናል—ፊልጵ. 3፡13፤ ዮሐ. 1፡16፤ ሮሜ 5፡21፤ 1 ጴጥ. 4፡10፤ ኤፌ. 3፡2።

መ. የእግዚአብሔር ሙሉ ማዳን በጸጋ ብዛት እና በጽድቅ ስጦታ ብዛት (ሮሜ. 5፡10፣17፣21) በክርስቶስ ሕይወት እንነግሥ ዘንድ በዚህ ሕይወት እንድንድን ነው፤ የጽድቅ ስጦታ የእግዚአብሔር ፍትሐዊ ቤዛነት ተግባራዊ በሆነ መንገድ በእኛ ላይ ሲተገበር ነው፤ ለሕይወታዊ ድነታችን ለሁሉ እንደሚበቃ አቅርቦታችን ጸጋ እግዚአብሔር ራሱ ነው።

**II. ራእይ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ የመጨረሻው መጽሐፍ፣ ድል ነሺዎቹን የሚመለከት መጽሐፍ ነው፤ በምዕራፍ 2 እና 3፣ የታላቁ አብርሃም መንፈሳዊ ዘሮች ለሆንን ለእኛ፣ ለአማኞች ሰይጣናዊዎቹን ቀውሶች በሙሉ (ተዛ. ቆላ. 1፡17፣ 18፣ 10)የሚያሸንፉ እና በመለኮታዊው ኢኮኖሚ (ሮሜ 8፡37፤ 2 ቆሮ. 2፡14) የሚያሸንፉ ድል ነሺዎች እንሆን ዘንድ ጌታ ሰባት እጥፍ ጥሪን ያስተላልፋል (2፡7፣ 11፣ 17፣ 26፤ 3፡5፣ 12፣ 21)፡-**

ሀ. ከእግዚአብሔር እይታ አኳያ አራት ዋና የሰው ዘሮች አሉ፡- የአዳም ዘር፣ በሥጋ የአብርሃም ዘር (ዘፍ. 13፡16)፣ በመንፈስ የአብርሃም ዘር (15፡5፤ ገላ. 3፡7፣ 29) እና የድል ነሺዎች ዘር፤ የእምነት መንፈሳችንን በማንቀሳቀስ በድል ነሺዎቹ ዘር ውስጥ እንደሆንን ማወጅ አለብን (2 ቆሮ. 4፡13)።

ለ. የራእይ መጽሐፍ ያለ ድል ነሺዎቹ ክርስቶስ ተመልሶ ይመጣ ዘንድ ምንም አይነት መንገድ እንደሌለ ያሳየናል፤ ክርስቶስ መንገዳችን (ዮሐ. 14፡6) እንደሆነ እናውቃለን፣ ነገር ግን ከልቡ ጥልቀት ክርስቶስ ለድል ነሺዎቹ የሚነግራቸው ነገር እነርሱ መንገዱ እንደሆኑ ነው፤ ድል ነሺዎቹ ክርስቶስ ተመልሶ የሚመጣበት ያ መንገድ ናቸው (ራእ. 19፡7-9፤ መዝ. 45፡13-14)።

ሐ. ዛሬ ድል ነሺ፣ የሚነግሥ ሕይወት የሚኖሩ ያደርጋችሁ ዘንድ እግዚአብሔር እንዲባርካችሁ ፍቀዱ፤ ይህ ልዩና ብቸኛ በረከት ለድሰታችን ራሱን ወደ ውስጣችን የሚያደልበት ዘላለማዊው የሦስታንዱ አምላክ በረከት ነው—ዘኁ. 6፡22-27፤ 2 ቆሮ 13፡14፤ ኤፌ. 1፡3፤ ገላ. 3፡14።

**III. የጌታ ድል ነሺዎች እንድንሆን በሕይወት እንነግሥ ዘንድ መለኮታዊ፣ መንፈሳዊ፣ ሰማያዊ እና ንጉሣዊ በሆነ ሕይወት ዳግም እንደተወለድን ልናይ ያስፈልገናል፤ ጌታ "በምድር ዘርን እንደሚዘራ ሰው የእግዚአብሔር መንግሥት እንደዚህ ናት" ብሎ ተናገረ—ማር. 4፡26፤ 1 ዮሐ. 3፡9፡-**

ሀ. የጌታ ወንጌል ውጤትና ግብ እና በዚህ ዘመን ያለችው ቤተ ክርስቲያን (ሮሜ 14፡17) የሆነው የእግዚአብሔር መንግሥት የሕይወት፣ የእግዚአብሔር ሕይወት ጉዳይ እንደሆነ በማመልከት የሚያቆጠቁጠው፣ የሚያድገው፣ ፍሬ የሚያፈራው፣ የሚበስለው፣ እና መከርን የሚያፈራው (1 ቆሮ. 3፡6-9፤ ራእ. 14፡4፣ 15-16) ይህ ዘር ወደ አማኞች ውስጥ የተዘራው የመለኮታዊው ሕይወት ዘር ነው (ቁ. 9፤ 1 ጴጥ. 1፡23)።

ለ. የእግዚአብሔር መንግሥት ክርስቶስ ራሱ ነው (ሉቃ. 17፡21)፤ እግዚአብሔር ወደ ሚገዛበት ክልል ለመዳበሩ (ማር. 4፡26-29፤ 1 ቆሮ. 3፡9) በእግዚአብሔር የተመረጡት ሕዝቡ ውስጥ እንዲያድግ፣ እንዲኖር እና እንዲገለጥ እርሱ በስብዕና ውስጥ እንዳለ ሦስታንዱ አምላክ (ቆላ. 2፡9) በእነርሱ ውስጥ የሚዘራ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘር፣ "ዘረ መል" ነው።

ሐ. የመላው አዲስ ኪዳን ውስጠ-መሠረታዊ ንጥረ-ነገር ሦስታንዱ አምላክ ወደ ተመረጡት ሕዝቡ ይዘራ እና በእነርሱ ውስጥ ወደ እግዚአብሔር መንግሥትነት ይዳብር ዘንድ ሥጋ መልበሱ ነው፤ የእግዚአብሔር ግብ የእግዚአብሔር መንግሥት ሙሉ መዳበር ነው፡-

1. በወንጌላት የመንግሥቱ ዘር፣ ዘረ-መል መዘራት አለን—ማር. 4፡3፣ 14፤ ማቴ. 9፡35።
2. በሐዋርያት ሥራ የመንግሥቱን ዘር፣ ዘረ-መል በተቀበሉ በሺዎች በሚቆጠሩ ዘሪዎች የዚህ መዘራት መስፋፋት እና መሰራጨት አለ—6፡7፤ 12፡24፤ 19፡20።
3. በመልእክቶች የመንግሥቱን ዘር፣ ዘረ-መል ማደግ እናያለን—1ቆሮ. 3፡6፣ 9፤ 2 ጴጥ. 1፡3፣ 11።
4. የዚህ ዘር መከር በራእይ መጽሐፍ ውስጥ በበኵራቱ መታጨድ እና በመከሩ ይገኛል—14፡4፣ 15-16፤ ማር. 4፡29፤ ማቴ. 13፡39።
5. የሺሁ ዓመት መንግሥት ከወልድ ጋር እንደ ንጉሥ እና ከድል ነሺዎቹ ጋር እንደ አብሮ-ነጋሾች፣ እንደ "የመንግሥቱ-ዘር ሕዝብ" የእግዚአብሔር መንግሥት ዘር፣ ዘረ-መል ፍፁም መዳበር ይሆናል—ራእ. 20፡6።
6. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መንግሥት የሆነችው አዲሲቱ ኢየሩሳሌም በናዝሬቱ ኢየሱስ በአራቱ ወንጌላት የተዘራ የመንግሥቱ ዘር፣ ዘረ-መል ሙሉ መዳበር ናት—ራእ. 21፡2፤ 22፡1፣ 3፣ 5፤ 5፡10፤ 3፡12፤ 11፡15፤ 19፡6፤ 20፡6፤ መዝ. 146፡10።
7. ዘመኑ ይጠናቀቅ ዘንድ ለመንግሥቱ ዘር፣ ዘረ-መል መሰራጨት እና መዳበር የመንግሥቱን ወንጌል ለመላው ምድር ለመስበክ ከጌታ ጋር አንድ መሆን ያስፈልገናል—ማቴ. 24፡14።

## IV. በልምምድ፣ በሕይወት መንገሥ ማለት በመለኮታዊው ሕይወት አገዛዝ ሥር መሆን ማለት ነው፡-

ሀ. በአብ የመለኮታዊ ሕይወት አገዛዝ ሥር በመሆን ክርስቶስ በሕይወት የመንገሥ ምሳሌ ነው—ተዛ. 8፡5-13።

ለ. ጳውሎስ በሕይወቱና በአገልግሎቱ በመለኮታዊው ሕይወት አገዛዝ ሥር የነበረ ሰው ምሳሌ ነው—2 ቆሮ. 2፡12-14።

ሐ. የጸጋን ብዛት እና የጽድቅ ስጦታን ብዛት የተቀበሉ አማኞች በሙሉ የመለኮታዊውን ሕይወት መገደብ እና መወሰን በተግባር የመለማመዳቸው አስፈላጊነት አለ፤ በመንግሥቱ አገዛዝ ሥር የሆነ ሕይወት የጽድቅ፣ የሠላም እና በመንፈስ ቅዱስ የሆነ ደስታ ሕይወት ነው፤ በዚህ መንገድ መኖር ክርስቶስን እንደ ባሪያ ማገልገል ነው፣ እንዲህ ያለው ሕይወት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ እና በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ያለው ነው—ሮሜ 14፡17-18፤ ተዛ. 1 ቆሮ. 12፡3።

## V. ዘዳግም ተገቢው ንጉሥ መጀመሪያ በእግዚአብሔር ቃል መማር፣ መመራት፣ መገዛት እና በቁጥጥሩ ሥር መሆን እንደነበረበት ይገልጣል (17፡14-15፣ 18-20)፤ በአብያተ ክርስቲያናት ባሉ ሽማግሌዎች እና በሕይወት የመንገሥ ፍላጎት ባለን በእኛም ዘንድ ይህ መርህ ያው መሆን አለበት (2 ጢሞ. 3፡14-17)፡-

ሀ. ቤተ ክርስቲያንን ያስተዳድሩ ዘንድ ሽማግሌዎች በእግዚአብሔር ቃል እንደገና መቀናበር አለባቸው (1 ጢሞ. 3፡2፤ 5፡17)፤ ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር አስተዳደር ሥር፣ በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር እና ቁጥጥር ሥር ይሆናሉ።

ለ. ያኔም በቅጽበት በውሳኔዎቻቸው ውስጥ እግዚአብሔር ይኖራል፣ ሽማግሌዎቹም የቤተ ክርስቲያን ጉዳዮችን ያስተዳድሩ ዘንድ እግዚአብሔርን ይወክላሉ፤ ይህ አይነት አስተዳደር የእግዚአብሔር አገዛዝ ሥርዓት ነው።

ሐ. በዕዝራና በነህምያ አመራር ሥር የተመለሱት የእስራኤል ሕዝብ የእግዚአብሔር ምስክር ሕዝብ ይሆኑ ዘንድ በቃሉ በጋራ በእግዚአብሔር አማካኝነት እና በእግዚአብሔር [እንደ ንጥረ-ነገር] እንደገና ተቀናብረው ነበር፤ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደገና ማቀናበር በቃሉ ይሞሉ ዘንድ ወደ እግዚአብሔር ቃል ውስጥ እነርሱን በመክተት እነርሱን ማስተማር ነው—ነህ. 8፡1-18።

መ. የእግዚአብሔር ቃል ከመንፈስ ጋር አንድ ነው (ዮሐ. 6፡63፤ ኤፌ. 6፡17)፤ መለኮታዊውን ቃል በየዕለቱ በማንበባችን አማካኝነት የእግዚአብሔር ቃል በውስጣችን ይሠራል፣ መንፈስም በቃሉ በኩል የእግዚአብሔርን ባሕሪ ከእግዚአብሔር ንጥረ-ነገር ጋር ወደ ማንነታችን ውስጥ በቅጽበት ያድላል፣ በእግዚአብሔር እንድንቀናበር ያደርገናል።

**VI. በሕይወት ለመንገሥ፣ በመንፈስ አመራር ሥር መሆን ጭምር ያስፈልገናል፤ የዮሴፍ ሕይወት ዘገባ የመንፈስ አመራር መገለጥ ነው፣ ምክንያቱም የመንፈስ አመራር የአንድ የበሰለ ቅዱስ የመንገሥ ገጽታ ነው፤ በመንግሥቱ እውነታ በመለኮታዊው ሕይወት መገደብ እና መወሰን ሥር በመሆን በሕይወት የመንገሥ ሕይወት ነው፣ ከማንኛውም ሌላ የመንፈስ ገጽታም የሚበልጥ ነው—ሮሜ 5፡17፣ 21፤ 14፡17-18፤ 1 ቆሮ. 2፡15-16፤ 2 ቆሮ. 2፡13-14፤ 3፡17-18፤ 2 ጢሞ. 4፡22፤ ራእ. 4፡1-3፡-**

ሀ. "ያ ባለ ሕልም" ዮሴፍ (ዘፍ. 37፡19) በእግዚአብሔር እይታ መሠረት የእግዚአብሔር ሕዝብ በሕይወት የተሞሉ የስንዴ ነዶዎች እና በብርሃን የተሞሉ ሰማያዊ ብርሃናት እንደሆኑ አየ (ቁ. 5-11)፤ ከእግዚአብሔር የሆኑት የዮሴፍ ሁለቱም ሕልሞች (ቁ. 7፣ 9) በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ባሕሪ፣ ስፍራ፣ አገልግሎት እና ግብ በተመለከተ የእግዚአብሔርን መለኮታዊ እይታ ገለጡለት።

ለ. የዮሴፍ ሕልሞች ሕይወቱን እና ባሕሪውን ተቆጣጠሩ፤ ዮሴፍ ባሕሪው የላቀና ድንቅ የነበረው በሕልሞቹ ባየው ራእይ መሠረት ስለተመራ ነው (ተዛ. ሐዋ. 26፡19)፤ ወንድሞቹ ንዴታቸውን ገለጡ (ዘፍ. 37፡18-31)፣ በሥጋዊ ምኞታቸውም ተዘፈቁ (38፡15-18)፣ ዮሴፍ ግን በሕይወት እንደተሞላ የስንዴ ነዶ በመመላለስ እና በጨለማ ውስጥ እንደሚያበራ ሰማያዊ ኮከብ ራሱን በመምራት ንዴቱን ተቆጣጠረ፣ የሥጋውንም ምኞት አሸነፈ (39፡7-23)።

ሐ. በሰማያዊው ራእይ ሥር የነበረው የዮሴፍ ሕይወት በማቴዎስ 5—7 የተገለጸው የመንግሥተ ሰማያት ሕይወት ነበር፤ እንዲህ አይነት ሕይወት በመኖር እንደ ንጉሥ ለመንገሥ ሙሉ በሙሉ ተዘጋጅቶ ነበር፤ በማቴዎስ ውስጥ በእነዚህ ምዕራፎች በተገለጠው በሰማያዊው መንግሥት ሕገ-መንግሥት መሠረት ንዴታችን መገዛት አለበት፣ ሥጋዊ ምኞታችንም መሸነፍ አለበት (5፡21-32)።

መ. እንደ በሰለው ሕይወት የሚያሸንፍ ገጽታ ወኪል ዮሴፍ የጌታን መገኘት፣ ከጌታ መገኘትም ጋር የጌታን ሥልጣን፣ ብልጥግና እና በረከት ተደሰተ—ዘፍ. 39፡2-5፣ 21፣ 23፤ ሐዋ. 7፡9።

ሠ. ምንም እንኳን ዮሴፍ ለወንድሞቹ በስብዕና ስሜቶች የተሞላ ቢሆንም ራሱን ከስሜቶቹ ሁሉ ጋር በመንፈስ አመራር ሥር ጠበቀ፤ ራሱን ካደ፣ ራሱን ፍጹም በሆነ መልኩ ለእግዚአብሔር እና ለሕዝቡ ፍላጎት በማስገዛት ራሱን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ አገዛዝ ሥር አደረገ—ዘፍ. 42፡9፣ 24፤ 43፡30-31፤ 45፡1-2፣ 24።

ረ. ዮሴፍ በአዲስ ኪዳን ለተገለጠው ነገር ሕያው ምሳሌአዊ ስዕል ነው፤ የግል ፍላጎት፣ የግል ደስታ፣ የግል ስሜት፣ የግል ምኞት ለማሳካት መፈለግ፣ ወይም የግል ግብ ያልነበረው ራሱን የሚክድ ሰው ነበር፤ ሁሉም ነገር ለእግዚአብሔር እና ለእግዚአብሔር ሕዝብ ነበር፤ የዮሴፍ ራስን መካድ፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ እጅ ሥር መገደብ የመንግሥቱን ሕይወት ለመለማመዱ ቁልፍ ነበር—ዘፍ. 45፡24፤ ማቴ. 16፡24፤ 2 ዜና 1፡10፤ ኢሳ. 30፡15፤ ፊልጵ. 1፡9፤ 1 ጢሞ. 5፡1-2፤ 1 ተሰ. 3፡12፤ 4፡9፤ 2 ተሰ. 1፡3፤ ሮሜ 12፡10፤ 1 ዮሐ. 4፡9፤ ዕብ. 13፡1።

ሰ. የዮሴፍ ግንዛቤ እርሱን ወደ ግብጽ የላከው እግዚአብሔር እንደነበር ነው፤ በዘፍጥረት 50፡20 ለወንድሞቹ "እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ፤ እግዚአብሔር ግን...ለመልካም አሰበው" አላቸው (45፡5፣ 7፤ 50፡19-21፤ ተዛ. 41፡51-52)፤ ይህ በሮሜ 8፡28-29 ያለው የጳውሎስ ቃል እውነታ ነው፤ ዮሴፍ ወንድሞቹ በእርሱ ላይ ያደረጉትን ነገር ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደተቀበለው አድርጎ ተቀበለው፣ የበደሉትን እነርሱንም አጽናና (ዘፍ. 45፡5-8፤ 50፡15-21)፤ ምን ዓይነት ጸጋ እና ምን አይነት የላቀ መንፈስ ነበረው!

ሸ. በሕይወት ከተሞሉ የስንዴ ነዶዎች እና በብርሃን ከተሞሉ ከዋክብት ውጭ ሌላ ምንም ነገር የሌለባትን አዲሲቱ ኢየሩሳሌምን በጊዜ ውስጥ አልፈን ለማየት "መለኮታዊ ቴሌስኮፕ" መጠቀም አለብን፤ በሕይወት አብልጠን በበሰልን መጠን ቅዱሳንን ሆነ ቤተ ክርስቲያንን በተመለከተ በአሉታዊ መልኩ መናገራችን ያነሰ ይሆናል—ተዛ. 38፡27-30፤ ማቴ. 7፡1-5፤ 1 ጴጥ. 3፡8-9።

**VII. በሕይወት የመንገሥን ግብ ማየት እና ወደዚህ ግብ መድረስ ያስፈልገናል፤ በመለኮታዊው ሕይወት አገዛዝ እየኖርን በሕይወት ስንነግሥ ውጤቱ በቤተ ክርስቲያን ሕይወት የሚገለጠው እውነተኛውና ተግባራዊው የአካሉ ሕይወት ነው—ሮሜ 12፡1-4፣ 9-12፣ 15-18፤ 14፡1-9፤ 15፡1-13፡-**

ሀ. ወደ ክርስቶስ ውስጥ እንዳመኑ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር የፍቅሩ ልጅ መንግሥት ፈልሰናል፣ በቤተ ክርስቲያን ሕይወትም ፍቅር ያሸንፋል (ቆላ. 1፡12-13)፤ አካሉ ራሱን በፍቅር ይገነባል (2 ቆሮ. 8፡1፤ ኤፌ. 1፡4፤ 3፡17፤ 4፡2፣ 15-16፤ 5፡2)፣ ፍቅርም ለቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ አካል መገንባት ምንም ነገር እንሆን ዘንድ እና ምንም ነገር እናደርግ ዘንድ እጅግ የላቀው መንገድ ነው (1 ቆሮ. 12፡31፤ 13፡4-8)።

ለ. ክርስቶስ እንደ ፍቅር ከሌለን ንግግራችን ሁሉ "እንደሚጮኽ ናስ" እና "እንደሚንሸዋሸዋ ጸናጽል" ሕይወት የማይሰጥ ድምጽ ነው—ቁ. 1።

ሐ. ቤተ ክርስቲያን የፖሊስ ጣቢያ ወይም ፍርድ ቤት ሳትሆን መንፈሳዊ ልጆችን ለማሳደግ አፍቃሪ መኖሪያ ቤት፣ የታመሙትን ለመፈወስ እና ለመመለስ ሆስፒታል እና ሌሎችን በፍቅር ለማስተማር ትምሕርት ቤት ናት—ማቴ. 9፡12፤ 2 ቆሮ. 11፡29፤ የሐ. 8፡7፣ 10-11፤ 1 ቆሮ. 9፡22፤ ሉቃ. 15፡1-7።

**VIII. በሕይወት ስንነግሥ ሳለን በውስጣችን ያደረውን ክርስቶስ በውስጣችን "ለዘላለም ሕይወት" እንደ ጸጋ እንዲነግሥ እየፈቀድን ነው፤ ይህ በሕይወት የመንገሥ መጠናቀቅ ነው—ዕብ. 4፡16፤ ሮሜ 5፡17፣ 21፦**

ሀ. ዮሐንስ 4፡14 "እኔ የምሰጠው ውኃ በእርሱ ውስጥ ለዘላለም ሕይወት የሚፈልቅ የውኃ ምንጭ ይሆናል" ይላል።

ለ. [በዮሐንስ 4፡14 "ለዘላለም" በሚለው ቃል ውስጥ] *ለ* (በሮሜ 5፡21 ውስጥ ያለውም *ለ*) መዳረሻን በተመለከተ ይናገራል፤ የዘላለም ሕይወት የሚፈስሰው ሦስታንዱ አምላክ መዳረሻ ነው፤ *ለ* በተጨማሪም "መሆን" ማለት ነው።

ሐ. የሚፈስሰውን ሦስታንዱን አምላክ—አብን እንደ የሕይወት መፍለቂያ፣ ወልድን እንደ ፍልቅ እና መንፈስን እንደ የሕይወት ውኃ ወንዝ—በመደሰት እንደ የእግዚአብሔር ሕይወት ጥቅል ድምር፣ የሕይወት ከተማ፣ አዲሲቱን ኢየሩሳሌም እንሆን ዘንድ የጸጋን ብዛት እየተቀበልን ነው፤ ስለዚህ በሕይወት የመንገሣችን ውጤት እና መጠናቀቅ ልዩና ብቸኛ እና ከፍተኛ-የመጨረሻ-ምርጥ እንደሆነው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ግብ—አዲሲቱ ኢየሩሳሌም መሆን አለበት።

© 2022 Living Stream Ministry